MCPS
ROCKVILLE, MARYLAND

# የማርከ መስጫ ክፍለ ጊዜ አንድ የ5ኛ ክፍል የወላጆች መመሪያ

በ1ኛ ማርከ መስጫ ወቅት፣ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለፁት ፅንሰሃሳቦች እና ክሂሎቶች ትምህርት ይቀበላሉ።

እባክዎ ልብ ይበሉ፡- በ ግራጫማ ቀለም/ከለር የታዩ ክህሎቶች እና ጽንሠ ሃሳቦች ትምህርት ተሰጥቷል ነገር ግን በሪፖርት ካርድ ላይ ማርከ አልተጻፈም።

## ሂሳብ 5/6

### መለካት እና የተመዘገበ መረጃ

- በአንድ የተሰጠ የመለኪያ ስርአት ውስጥ የተለያየ-መጠን ያላቸው ደረጃቸውን የጠበቁ መስፈርቶች መካከል መቀያየር።
- የአንድ አካል ክፍልፋዮችን እየተለካ የተመዘገበ መረጃ/ዳታ ለያይቶ ለማሳየት መስመር ተጠቀም(ሚ) እና ስለ መረጃው/ዳታ ፕሮብሌሞችን ለመፍታት አራቱን የስሌት ምልክቶች ተጠቀም(ሚ)።

### ቁጥሮችና ግብረቶች በአስሮሽ ቤት

- ባለ በርካታ-አሃዝ ሙሉ ቁጥሮችን በመደበኛ የስሌት ዘዴ/algorithm በቅልጥፍና ማባዛት።
- ተጨባጭ የሆነ ቅርፅ/ሞዴል፣ ወይም ስእል እና የቦታ ስልቶችን መሰረት በማድረግ፣ የግብረቶች ጠባዮች፣ እና/ወይም በመደመር እና በመቀነስ መካከል ባለዉ ግንኙነት፤ ዴሲማሎችን ወደ መቶኛዎች መደመር፣ መቀነስ፣ ማባዛት፣ ማካፈል እና ስልቱን ከተፃፈ ዜደ ጋር ማዛመድ እና የግልጋሎቱን/ጥቅም ላይ የዋለዉን ምክንያት መግለፅ።

### ቁጥሮች እና ስሌቶች-ክፍልፋዮች

- በክፍልፋዮች ወይም ድብልቅ ቁጥሮች ፎርም ለሚይዙ መልሶች የሚያመሩ የሙሉ ቁጥሮች ማክፈልን የሚያካትቱ የቃል ፕሮብሌሞች መፍታት።
- አንድን ክፍልፋይ ወይም ሙሉ ቁጥር በክፍልፋይ ማባዛት።
- የአሃድ ክፍልፋዮችን በሙሉ ቁጥሮች እና ሙሉ ቁጥሮችን በአሃድ ክፍልፋዮች ያካፍሉ።
- የክፍልፋዮችን እና የተደባለቁ ቁጥሮችን ብዜት በመጠቀም ተጨባጭ-ፕሮብሌሞችን ፍታ/ቺ።

## ምንባብ

### የማንበብ ግንዛቤ፡- ስነ ፅሁፍ

- አንድ ፅሁፍ በግልጽ ምን እንደሚል በሚገለፅበት ጊዜ እና ከፅሁፍ ሃሳቦች በሚወሰዱበት ጊዜ በትክክል መጥቀስ።
- በታሪኩ ውስጥ ያሉ ገጸ-ባህሪያት ለአዳጋች ሁኔታዎች እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡን ጨምሮ፣ ከጽሑፍ ዝርዝር ላይ የታሪኩን ጭብጥ ይለዩ።
- በጽሑፍ ውስጥ በተወሰኑ ዝርዝሮች ላይ በማተኮር፣ በአንድ ታሪክ ውስጥ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ገጸ-ባህሪያትን፣ ቅንብሮችን/መቼት፣ ወይም ክዋኔዎችን ማወዳደር እና ማነጻጸር።
- ተከታታይ ምዕራፎች እርስ በርሳቸው ተገጣጥመው የአንድ ልዩ ታሪክ አጠቃላይ መዋቅር እንዴት እንደሚሰጡ ማብራራት።
- የተራኪ ወይም የተናጋሪ አመለካከት በሁኔታዎች አገላለጽ ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ ግለጽ/ጪ።
- በ5ኛ ክፍል ደረጃ በሚገባ ውስብስብ የሆነ ስነ-ጽሑፍን አንብቦ መገንዘብ።

### ምንባብ የመረዳት (የማወቅ) ችሎታ፡- መረጃዊ

- ፅሁፉ በግልፅ የሚለውን ሲያብራሩ እና ከፅሁፉ መረጃ ሲወስዱ ከፅሁፉ በትክክል መጥቀስ።
- ከተከታታይ የፅሁፍ መዋቅር ጋር በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ፅሁፎች የቀረቡ አጠቃላይ የክውነቶች፣ አስተያየቶች፣ጽንሰ ሀሳቦች ወይም የመረጃዎች መዋቅር ማወዳደርና ማነፃፀር።
- በሚወክሉት አስተያየት ውስጥ አስፈላጊ ተመሳሳይነቶችንና ልዩነቶችን እያመላከቱ፣የተመሳሳይ ክውነት ወይም ርእስ በርካታ ትረካዎችን መተንተን።
- ለ5ኛ ክፍል በአግባቡ ውስብስብ የሆነ መረጂያዊ ፅሁፍ ማንበብና መገንዘብ።

### ቋንቋ፡- የቃላት ዝርዝር ግኝት እና አጠቃቀም

- ስለ 5ኛ ክፍል ርእሶችና ፅሁፎች፣ በሌሎች አስተሳሰቦች ላይ እየገነቡ እና የየራሳቸውን በግልፅ እየገለፁ በትብብሮሽ ውይይቶች ስብስብ በውጤታማነት መሳተፍ።
- ድምፅ ከፍ ተደርጎ የተነበበ ፅሁፍን ወይም በተለያዩ ሚድያና፣ በሚታይ፣ የብዛት እና የቃልን የሚያካትቱ ቅርፀቶች የቀረበ መረጃን ማጠቃለል።

## ጽሑፍ

### ትረካ

- እውነተኛ ወይም ሃሳብ የወለዳቸው ተሞክሮዎችን ወይም ክውነቶችን ለማዳበር በውጤታማ ቴክኒክ፣ ገላጭ ዝርዝሮች፣ እና በጠሩ የክዉነት ቅደም-ተከተሎች በመጠቀም ትረካ መጻፍ።
- ሁኔታዎችን በማመቻቸት ተራኪ እና / ወይም ገጸ-ባህሪያትን ማስተዋወቅ፤ በተፈጥሮ የሚገለፀውን የክስተት ቅደም ተከተል ማደራጀት፤ ታሪኮችን እንደ ውይይት፣ መግለጫዎች፣ እና በመንቀሳቀስ/በዝግታ አቀራረብ የመሳሰሉ ትረካዊ ቴክኒኮችን መጠቀም፣ እና ከተረኩባቸው ልምዶች ወይም ክስተቶች የተገኘውን መደምደሚያ ማቅረብ።

### ትምህርት ሰጭ/ገላጭ

- እንድን ርእስ ለማገናዘብና አስተያየትንና መረጃን በግልፅ ለማስተላለፍ መረጂያዊ/ገላጭ ፅሁፎች መፃፍ።
- አንድን ርእስ በግልፅ ማስተዋወቅ፤ አጠቃላይ ትዝብትና ትኩረት መስጠት፤ ርእሱን ከሃቆች፣ ፍቺዎች፣ ጭብጥ ዝርዝሮች፣ ጥቅሶች፣ እና ከቡድን-ጋር-የተዛመዱ መረጃዎች ጋር በሎጂክ ማዳበር፤ ማጠቃለያ አረፍተሃሳብ ወይም ክፍል መስጠት፤ ቅርፀቶች (ለምሳሌ፣ አርእስቶች)፣ ስእሎች እና ባለበርካታ-ሚድያን ግንዛቤን ለማገዝ ጠቃሚ ከሆነ፣ ማካተት።

### አስተያየት

- በርእሶች ወይም በፅሁፎች ላይ በምክንያቶችና በመረጃዎች እየደገፉ የአመለካከት አጫጭር ድርሰቶችን አስተያየት ፃፍ/ፊ።
- ሃሳብን ለመግለጽ፣ በአመክንዮ/አሳማኝ/ተቀባይነት ባላቸው ምክንያቶች ማስረጃ እና በዝርዝር የተደገፈ መደምደሚያ ወይም ክፍል፣ እና ሃሳቦቹ የጸሐፊውን ዓላማ ለመደገፍ በምክንያታዊነት የተቧደኑ መሆናቸውን ድርጅታዊ መዋቅር በፍጠር አንድን ርእስ ወይም ጽሑፍ በግልጽ አስተዋውቅ(ቂ)።

### ሂደት፣ ውጤት፣ ጥናት/ምርምር

- እድገቱና አደረጃጀቱ ለተግባር፣ አላማ፣ እና ለአድማጭ ተገቢ የሆነ ጥራት ያለውና ስሙሙ ፅሁፍ ማቅረብ።
- ከእኩዮችና ከአዋቂዎች የተወሰነ አመራርና ድጋፍ ጋር፣ ፅሁፍን ለማፍለቅና ለማተም እንዲሁም ከሌሎች ጋር ለመገናኘትና ለመተባበር በቴክኖሎጂ፣ ኢንተርኔትን ጨምሮ፣ መጠቀም።
- ለተለያዩ ሥርዓት-ተኮር ተግባራት፣ አላማዎች እና ታዳሚዎች ዳጋግሞ ለረጅም የጊዜ መቃኖች (የምርምር፣ ማሰላሰያ፣ እና የክለሳ ጊዜ) እና አጠር ላሉ የጊዜ መቃኖች (ለአንድ-አፍታ ወይም ለአንድ ወይም ሁለት ቀን) መፃፍ።

### የቋንቋ አጠቃቀም

- ዋነኛ አስተሳሰቦችን ወይም ዘውጎችን ለመደገፍ በአንድ ርእስ ወይም ፅሁፍ ዘገባ ማቅረብ ወይም አስተሳሰቦችን በሎጂክ ቅደም-ተከተል በመስጠት እና በተገቢ ሃቆችና አስፈላጊ፣ ገላጭ ዝርዝሮች በመጠቀም፣ አንድ ሃሳብ ማቅረብ፤ ሊገባ በሚችል ፍጥነት በግልጽ ይናገሩ።
- የዋነኛ አስተሳሰቦች ወይም ዘውጎች እድገትን ለማበልፀግና መግለጫ ሲሰጥ ተገቢ ሲሆን ባለ-በርካታ-ሚድያ (ለምሳሌ፣ ግራፊኮች፣ ድምፅ) እና የሚታዩ ትርእይቶች ያካቱ።
- በመፃፍና በንግግር የመደበኛ እንግሊዘኛ ስዋስውና አጠቃቀም ደንቦች በቂ ችሎታ ማሳየት።

## ሳይንስ

### ፊዚካል ሳይንስ

- ቁሳቁሶችን በጠባያቸው በመመስረት ለመለየት ትዝብቶችንና መለካቶችን ማድረግ።
- አንድ ቁስአካል ሲግል፣ ሲቀዘቅዝ፣ ወይም የተለያዩ ነግሮች ሲቀላቀሉበት ለውጦች ቢኖሩም አጠቃላይ ክብደቱ እንደተጠበቀ እንደሚቆይ ማረጋገጫ ለመስጠት አንድን ቁስአካል ብዛት እየለካህ(ሽ) በግራፍ አሳይ።
- ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ነገሮች ቢደባለቁ አዲስ ነገር ይፈጥሩ እንደሆነ ለመወሰን ምርመራ ማካሄድ።

### ምህንድስና ንድፍ እና ሂደት

- ለቋቁሶች፣ ጊዜ፣ ወይም ዋጋ ስኬትና ማእቀቦች የተለዩ መስፈርቶችን የሚያካትት አንድን ችግር ወይም ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ቀላል የንድፍ ፕሮብሌም መበየን።
- ለአንድ ፕሮብሌም በርካታ መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ፣ እያንዳንዳቸው የፕሮብሌሙን መስፈርቶችና ግዴታዎች እንዴት እድርጎ አሳምሮ እንደሚያሟላ መሰረት በማድረግ፣ ማፍለቅና ማወዳደር።

- ተለዋጮች ቁጥጥር ስር የሆኑባቸውና የመውደቂያ ነጥቦች መሻሻል የሚችሉ የሞዴል ወይም የፕሮቶታይፕ ገፅታዎችን ለመለየት የሚታሰቡበት ፍትሃዊ ፈተናዎች ፕላን ማድረግና ማከናወን።

## ማህበራዊ ጥናቶች

### ሙዓለ-ነዋይ/ኤኮኖሚክስ

- በአሜሪካ የቅኝ ግዢ ወቅት ከሸቀጦችና ከአገልግሎቶች የኤኮኖሚ ፍላጎቶች አንፃር የሃብቶች/መገልገያዎች እጠረት በመኖሩ ሰዎች ምርጫዎች ማድረግ እንደነበረባቸው ማብራራት።
- በኮሎንያል አሜሪካ የኤኮኖሚ አቅጣጫ/ሲስተም እንዴት እንደሆነ መግለጽ።

## የመረጃ/ኢንፎርሜሽን ማንበብ እና መጻፍ/መሰረታዊ ትምህርት

- የተፈላጊ መረጃን ግኝቶች/መደምደሚያዎች ለማጋራት ለማዘጋጀት በተለያዩ ቅርፀቶች መጠቀም።
- የምንጭ ዝርዝር ለመፍጠር ተገቢ እና ተቀባይነት ባገኘ የመጥቀሻ ዘይቤ መጠቀም።

## ስነጥበብ

### ስነጥበብን መፍጠርና መገናኘት

- በስነጥበብና በሌሎች መስኮች አስተያየቶችን ለመተርጎምና ለመግለፅ የሚታዩ የስነጥበብ ሂደቶች መምረጥና አገልግሎት ላይ ማዋል።
- የስነጥበብ ንጥረነገሮችን እና የንድፍ መርሆዎችን ማደራጀት፡- ቅርፀት፣ ድግግሞሽ፣ ንፅፅር፣ ምት፣ እንቅስቃሴ፣ ሚዛን፣ አንድነት፣ እና አፅንኦት ለታዘቡት ወይም ላዩት ማላሽ ስነጥበብን ለመፍጠር።

### ስነጥበብን ማቅረብና ምላሽ መስጠት

- የሰዎች፣ እንስሶች፣ እና የነገሮች አካላዊ ጠባዮች በስነጥበብ ንጥረ ነገሮች እንዴት እንደሚወከሉ መተንተን።
- በዘውግ፣ ይዘት፣ ፎርም፣ እና በዘይቤ ተመሳሳይነቶችንና ልዩነቶችን ለመወሰን የተለያዩ የስነጥበብ ስራዎችን መተንተን።

## ሙዚቃ

### ሙዚቃ መጫወት

- ሌሎች ተማሪዎች ሲዘምሩ ወይም ተነጻጻሪ ክፍሎችን ሲጫወቱ በቀላል የክር ኣጃቢ መጫወት።
- በቡድኖች ውስጥ ሆኖ መዘመር፣ ተምቡሮችን በመደባለቅ እና ዳይናሚክ ደረጃዎችን በማጋጠም።

### ለሙዚቃ ምላሽ መስጠት

- የተወሰኑ መሳርያዎችን በማየትና በማዳመጥ መለየት።
- ምርጥ ስራዎች ደረጃውን ከጠበቀ የሙዚቃ ስነፅሁፍ እንዴት ከልዩ ታሪካዊ ክውነቶች ጋር እንደሚዛመዱ ማዳመጥና መግለፅ።

## የአካል ማጠንከርያ ትምህርት

### ጤና-አራማጅ አካላዊ ብቃትና እንቅስቃሴ

- በታለመው የልብ ምት ውስጥ ያሉ እንቅስቃሴዎችን ያስሉ እና ያከናውኑ።
- ደረጃውን የጠበቀ የአካል ብቃት ፈተናን በመጠቀም፣ ስርዓት ባለዉ አቀራረብ አማካኝነት የራስ የልብና የመተንፈሻ አካላዊ ብቃትን መገምገም።
- ግላዊ የጡንቻ ሃይል፣ የጡንቻ ጥንካሬ፣ እና የመተጣጠፍ ችሎታን ማገናዘብና ማወዳደር።

### የእንቅስቃሴ ክሂሎቶች እና ፅንሰሃሳቦች

- በመያዝ፣ መግፋት፣ እና መወርወር ላይ የሚያስፈልጉ ክሂሎቶችን ማጣራት።
- በእጅ ወይም በእግር እያነጠርከ(ሽ) ኳስ መቆጣጠር እንደምትችል/እንደምትችይ አሳይ።

## የጤና ትምህርት

### የአእምሮና የስሜት ጤንነት (MH)

- ውጤታማ የመግባባት ችሎታዎችን መገንዘብና ተግባር ላይ ማዋል።
- ለተለያዩ ሁኔታዎች ስሜቶችንና ምላሾችን ማገናዘብ።

### ኣልኮል፣ ትምባሆ እና ሌሎች እፆች Alcohol, Tobacco, and Other Drugs (ATOD)

- ሃኪም ለሚያዝቸው መድሃኒቶችና የOTC እፆች ሰላማዊ ልምዶችን መለየት።
- ማሪዋናን አእምሮ-የሚያዛባ/psychoactive ህገ ወጥ እፅ መሆኑን መለየት።
- ትምባሆ/ሲጋራ፣ አልኮል፣ እና ማሪዋና (አደንዛዥ እፅ) እንድትጠቀም(ሚ) የሚደረግብህ(ሽ)ን ግፊት የመቋቋም ችሎታን በማዳበር ክህሎት ተጠቀም(ሚ)።